ECD ETHIOPIAN CENTER FOR DEVELOPMENT

# ኢትዮጵያንሴንተርፎርዲቨሎፐመንት
# Ethiopian Center for Development

Tel. +251-11-6639516/17 Fax: +251+11-6639515 e'mail: haregashenafi2007@ethionet.et

ቀን፡ ህዳር 22,2018 ዓ.ም

ቁጥር፡ ecd/493/25

ለአዳማ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡ <u>ድርጅታችን በአዳማ ከተማ በሥራው ላይ ያጋጠመው ችግር እንዲፈታልን ስለመጠየቅ ስለመጠየቅ፤</u>

ኢትዮጵያን ሴንተር ፎር ዴቨሎፐመንት አገር በቀል የሲቪል ማኅበረሰብድርጅት ነው፡፡ ማዕከላችን እ.ኤ.አ ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ በአዳማ ከተማ በዳቤ ቆጨና በሶሎቄ ኩርፋ በሁለቱም ት/ቤቶች ቅጥር ግቢ ውስጥ የቅድመ መደበኛ ትምህርት የማስተማሪያ ሁለት ክፍሎች ያሉት ህንፃዎችን በመገንባት እና ቀጥሎ የተዘረዘሩትን የውስጥና የውጭ ዕቃች አሟልቶ ያስረከበ ሲሆን፡-

- የተማሪች ወንበርና ጠረጴዛ
- የመምህራን ወንበር፣ ጠረጴዛ እና የመጻሕፍት መደርደሪያች
- የህፃናት የደንብ ልብሶችን
- ለሕጻናቱ መማሪያ የሚሆን ሜንቶሶሪ
- የውስጥና የውጭ መጫወቻችን በማሟላትእና
- የቅድመ መደበኛ አመቻቾችን በማሰልጠን የቅድመ መደበኛ ትምህርቱ የተሳለጠ እንዲሆን ድርጅቱ የበኩሉን አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡

በተጨማሪም በአዳማ ከተማ በቦሰትና በሐዋዝ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሚገኙ ተማሪችን ለመርዳት የቲቶሪያል ትምህርት እና የትምህርተ መርዕድ ድጋፍ በማድረግ ሴት ተማሪች የተሻለ እውቀት እንዲኖራቸው ትልቅ ሥራ ሰርቷል፡፡

ድርጅታችን ኢትዮጵያን ሴንተር ፎር ዴቨሎፐመንት ከላይ በተጠቀሱት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሚገኙ ተማሪችን ከትምህርታቸው ጎን ለጎን የስራፈጠራ ክህሎት ሥልጠና እንዲያገኙ በማሰብ በአይነቱ የመጀመሪያ የሆነ ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪች በሚመጥን መልኩ በከፍተኛ ባለሙያች ጥናት አስደርጎ የኢንተርፕረነራዊ አስተሳሰብ ሥልጠና መማሪያ መጽሐፍ አዘጋጅቷል፡፡ ይህንንም መጽሐፍ በመጠቀም የሥራ ፈጠራ ሥልጠና ለመምህራን እና ለተማሪች በማሰልጠን ተማሪች በሰለጠኑት መሠረት የራሳቸውን የቢዝነስ ዕቅድ አዘጋጅተው ለውድድር እንዲቀርቡ በማድረግ ለአሸናፊች የማበረታቻ ሽልማት ሌሎችን በሚያስተምር መልኩ ተሰጥቷል፡፡

ከላይ ከዘረዘርናቸው ሥራች በተጨማሪ ድርጅታችን 10ኛ እና 12ኛ ክፍል አጠናቀው ትምህርታቸውን በተለያየ ምክንያት መቀጠል ላልቻሉ በድህነት የኑሮ ሁኔታ ውስጥ ላሉ ወጣት የከተማው ችግረኛ ወጣቶችን አዋጭ እና በቀላሉ የሥራ ዕድል ሊያስገኝላቸው የሚያስችል የሙያ ሥልጠና ለመስጠት ካለው ፅኑ ፍላጎት የተነሳ ለወጣቶች የሙያ ሥልጠና አገልግሎት የሚሰጥ የሥልጠና ማዕከል ለመገንባት ህጋዊ ሒደቶችን ተከትሎ ለከተማው አስተዳደር ባቀረበው ጥያቄ መሠረት በዚሁ ከተማ ቀበሌ 04 ውስጥ በሚገኘው በቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ግቢ ውስጥ ማዕከሉን እንዲገነባ በተፈቀደው መሠረት ከጃፓን ኤምባሲ ባገኘው ድጋፍ አስገንብቶ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የአስተዳደር አካላት በተገኙበት በማስመረቅ ሥራውን በተሳካ መልኩ ህጋዊ ሂደቶችን በመከተል